# የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና ለችግሩ አስተዋፅኦ ያላቸው ምንጮች፤

በላይ አለሙ 12-15-15

እንደሚታወቀው ሃገራችን ኢትዮጵያ በተለይ ላለፉት 10 እና 11 ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ትገኛለች፡፡ ለዚህ እድገት ዋነኛ ምንጭም መንግስት ቁርጠኛ የሆነ አቋም በመውሰድ ማንኛውም በኤኮኖሚው እንቅስቃሴ ለሚሳተፍ አካል አበረታች የሆነ ፖሊሲ ቀርፆ በመተግበሩ ነው፡፡ በተለይ የሃገራችን ኤኮኖሚ በእርሻ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን አብዛኛው የህብረተሰቡ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ ፖሊሲ በሰፊው መተግበሩ ለፈጣን የኤኮኖሚ እድገት ወሳኝ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ለኤክስፖርት ዘርፍ የተሻለ ድጋፍ ስለተደረገም የውጭ ምንዛሪ ምንጫችን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ለውጥ ማሳየቱም መንግስት ወደ ውጭ ለሚላኩ የእርሻ ውጤቶች ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ ነው፡፡ ሆኖም የተመዘገበው እድገት እስከነችግሮቹ መሆኑ በእድገቱ መጠን ተፅእኖ አድርገዋል፡፡ የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ በየግዜው የሚታየው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ዋና ዋና መንስኤዎች ለሚመለከተው አካል እንደግብአት ለማቅረብና ከግዜ ወደ ግዜ ችግሩ እየጨመረ የሄደው ነገር ግን መፍትሄ ሊበጅለት ያልቻለ በባንኮችና በነጋዴዎች መካከል ያለው የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ከምንጩ ለማድረቅ ምን መደረግ አለበት የሚለው ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡

አንድ ሃገር በሚያካሂደው ሁለንተናዊ(የኤኮኖሚ፣ የማህበራዊ የቴክኖሎጂ እንዲሁም ማንኛውም የመሰረተ ልማት) እድገት ወሳኙ ነገር ከውጭ ሃገር ለሚገዙ እቃዎች ወይም መሣሪያዎች መግዣ የሚውል በቂ የሆነ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ ሃገራችን ኢትዮጵያም ለበርካታ ሺህ አመታት የኋላ የእድገት አዙሪት ገብታ በመቆየትዋ ለሃገር ውስጥ ፍጆታ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በሌሉበት ሁኔታ ከቀላል እቃዎች እስከ ከባድ የፋብሪካ መሣሪያዎች ከውጭ ገዝታ ለማስገባት የግድ በቂ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ያስፈልጋታል፡፡ ነገር ግን ባለፉት የዕድገት ዓመታ የታየው ትልቁ ተግዳሮት በየግዜው እየጨመረ የመጣው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ነው፡፡ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት የውጭ ምንዛሪ ክምችት አስተማማኝ ለማድረግ መንግስት ወደ ውጭ ልከው የውጭ ምንዛሪ ለሚያስገቡ ባለሃብቶች የማበረቻቻ ስርዓት ዘርግቶ ተግባር ላይ አውሏል፡፡ ይህን የማበረታቻ ስርዓት ተጠቅመው በርካታ ዜጎች ወደ ሥራ እንዲገቡ በመደረጉ ከቡና ብቻ ይገኝ የነበረው የውጭ ምንዛሪ ሌሎች በርካታ የእርሻ ውጤቶች ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ገቢያችን እድገት አሳይተዋል፡፡ እርግጥ ለውጭ ምንዛሪ እጥረት ምንጮች የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እድገቱ ያመጣው ራሱ አንድ ምንጭ ቢሆንም በተለይ ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ለውጭ ምንዛሪ ትልቁ ምንጫችን የቡና ዋጋ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ መቀነሱ አንድ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቡናን እየተኩ እየመጡ ያሉት ሌሎች የእርሻና የማዕድን ውጤቶች ክፍተቱን ይሞሉታል ተብሎ ስለሚታሰብ ማነቀው የት ነው ያለው ተብሎ በደንብ መለየት ይኖርበታል፡፡

እንደኔ እምነት ማነቀው/ችግሩ የተዘረጋው የማበረቻች ስርዓት በራሱ በሂደት ክፍተቶችን እየፈጠረ ስለሄደ ነው፡፡ እነዚህ ክፍተቶች በሁለት መልኩ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛ ዓለም አቀፍ የንግድ ውድድር የፈጠረው ሲሆን ሁለተኛውና የሃገራችን ከፍተኛ የፈጣን ዕድገት ሳንካ የሆነው የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርበሰፊው መንሰራፋቱ ነው፡፡

1. **የዓለም አቀፍ ውድድር የፈጠረው ችግር**

   በርካታ የአለማችን ሃገራት የኤኮኖሚ እድገት መነሻቸው እርሻ በመሆኑ ለዚህ ዘርፍ የሚሰጡት ትኩረት የተነሳ የእርሻ ምርታማነት በማሳደግ ወደ ውጭ የሚልኩት ምርት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በተለይ ሃገራችን ኢትዮጵያ የምትታወቅባቸው የሰሊጥና የቡና ምርት ማንሳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በአፍሪካ፣ በደቡብና መካከለኛ አሜሪካ እንዲሁም በህንድ የሚመረቱ ምርቶች የማምረቻና የመሸጫ ዋጋቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በርካታ የኢትዮጵያ ምርት ገዢዎች ወደነዚህ ተወዳዳሪ ሃገራት ፊታቸውን ያዞራሉ፡፡ በመሆኑም ላኪዎቻችን በወረደ ዋጋ እንዲሸጡ ይገደዳሉ፡፡ ይህ በመሆኑ በርካታ የሃገራችን ላኪዎች ወደ ውጭ ልከው የሚያገኙት ኪሳራ ካልሆነ ትርፍ የሚባል የማይታሰብ ነው፡፡ ምናልባት አንዳንድ ላኪዎች የሰራተኞች ደሞዝና የባንክ ወለድ እስከ ከፈሉ ድረስ በገዙበት ዋጋ ቢሸጡ በንግዱ ዘርፍ

ለመቆየት ይመርጡ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አንድ ድርጅት በየዓመቱ እየከሰረ ከሄደ ወይም ትርፍ የማያገኝ ከሆነ እንዴት ሊኖር ይችላል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይገባል፡፡ እውነታው ግን ብዙዎቹ እየከሰሩም ቢሆን ለበርካታ ዓመታት ከንግዱ ዓለም ሊወጡ አልፈለጉም፡፡ ለምን?የዚህ ዋናው ምክንያት እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

## 2. የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባራት

እንደሚታወቀው መንግስት ኤክስፖርትን ለማሳደግ ሲል በርካታ ማበረታቻዎችን ተግባር ላይ አውሏል፡፡ ከነዚህም መካከል ከተለያዩ የታክስና ግብር ክፍያ ነፃ ማድረግ፣ ኤክስፖርት የሚሆኑ ምርቶች የሚያመርት ከቀረጥ ነፃ ግብዓት ከውጭ እንዲያስገባ፣ ወደ ውጭ ከተላከው ምርት የሚገኝ የውጭ ምንዛሪ እንደአግባብነቱ ቅድሚያ ተሰጥቶ ከውጭ ምርት እንዲያስገቡበት ላኪዎች እድል የተሰጠበት እንዲሁም ሌሎች ሊገለፁ ይችላሉ፡፡ ለዚሁ ፅሁፍ መነሻ የሆነውን የመጨረሻው የማበረታቻ ስርዓት የፈጠረው ክፍተት በመሆኑ እዚህ ላይ ላተኩር፡፡

### 2.1. በባንኮች ያለው የውጭ ምንዛሪ አመዳደብ ልዩነት

የውጭ ምንዛሪ ችግር ዋነኛ ምንጭ የሆነው በግል ባንኮች እየተተገበረ ያለው ፖሊሲ ነው፡፡ አንድ ላኪ ያስገባውን የውጭ ምንዛሪ ተመልሶ ለኢምፖርት ሊጠቀምበት እንደሚችል መደረጉ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸውም የሌላቸውም ምርቶች ከውጪ ያስመጣበታል፡፡ እራሱ ማስመጣት ካልቻለም የውጭ ምንዛሪው ለሌሎች አስመጪዎች እንዲያዞረው ይፈቀድለታል፡፡ ሃገራችን በውጭ ምንዛሪ እጥረት በምትሰቃይበት ሁኔታ ይህ የውጭ ምንዛሪ የኔ ነው ከፈለኩ አስቀምጠዋለሁ ከፈለኩ የፈለኩትን እቃ አስመጣበታለሁ አልያም እሸጠዋለሁ የሚል መረኑ የለቀቀ አመለካከት እንዲሰፍን መደረጉ በባንኮችና በነጋዴዎች ምን ያክል የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ እንደሰፈነ ያሳያል፡፡ ዜጎች የውጭ ምንዛሪ እኩል ተካፋይ ሆነው ስራን ለመስራት ባለመቻላቸው የሚያነሱት የመልካም አስተዳደር ችግርም አንዱ ይኸው ነው፡፡

### 2.2. ከውጭ ለሚገባ እቃ የሚከፈለው ዋጋ

በሃገራችን ጎልቶ የሚታየው የንግድ ባህል ማንኛውም በአስመጪነት የተሰማራ ድርጅት የግድ በላኪነት መሰማራት ይኖርበታል፡፡ ሆኖም አብዛኛው በውጭ ንግድ የሚሰማራው ዘርፍ አተርፍበታለሁ ብሎ ሳይሆን ከውጭ እቃ የሚያስመጣበት የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ስለሚሆንለት ብቻ ነው፡፡ በኢምፖርትና ኤክስፖርት ያለው የትርፍ ህዳግ (Margin) ልዩነት በጣም ከፍተኛ በመሆኑም በኢምፖርት የሚገኘውን ትርፍ ስለሚያጓጓ ከፍተኛ ዋጋ በመቀነስ ኤክስፖርቱን በተገኘው ዋጋ ያጣጡፉታል፡፡

ከዚህ ጋር ተይዞ የውጭ ምንዛሪ ከተፈቀደ በኋላ ከውጭ ለሚገዙ ምርቶች ከፍተኛ ዋጋ ይከፈልባቸዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ዋጋ የእቃው ትክክለኛ ዋጋ ላይሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ኩባንያዎች በውጭ ሃገር በተለይ በዱባይ ድርጅት በማቋቋም ወደ ሃገር ውስጥ የሚያስገቡት ምርት ከነዚህ ድርጅቶች በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እቃ እንዲገዛ ያደረጉና ወደ ድርጅታቸው የገባ የውጭ ምንዛሪ በውጭ በከፈቱት ሂሳብ ያከማቻሉ፡፡ በአንፃሩ ከኢ/ያ ወደ ውጭ የሚላ ምርቶች በርካሽ ዋጋ ይሸጣሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው የሃገሪቱ የውጭ ምንዛሪ በሁለቱም በኩል ወደ ውጭ ያሸሹታል ማለት ነው፡፡

### 2.3. የቅድመ ጭነት ብድር አጠቃቀም

መንግስት ያስቀመጠው ሌላው ማበረታቻ የቅድመጭነት ብድር ያለምንም ዋስትና መፍቀድ ነው፡፡ ይህ ማበረታቻ ወሳኝና ትክክለኛ ነው፡፡ ነገር ግን አጠቃቀሙ ላይ የከትትል ጉድለት ይታይበታል፡፡ ባለፉት 5 ና 6 ዓመታት ላኪዎች የተፈቀደላቸው የቅድመ ጭነት ብድር ከደንበኞቻቸው ጋር የገቡትን የግዥና ሽያጭ ውል ለባንኮች በማሳየት ወደ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚገኘው የpay in account ካስገቡ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ብሩን ወደኦቨር ድራፍት ሂሳብ (OD Account) በመመለስ ከውጭ ምርት የሚያስገቡበት ሁኔታ እንዳለ ሁሉም የሚያውቀው ሃቅ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቅድመ ጭነት

ብድር ከተወሰደ ማንኛውም ዓይነት የውጭ ሽያጭ ሂደቱ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሆን ያስገድዳል፡፡ ነገር ግን ላኪዎች ሂደቱ ወደ ግል ባንኮች ካዞሩ በኋላ ከዚህ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ እስከፈለጉት ድረስ ያገላብጡታል፡፡ ይህ የመረጡበት ሁኔታ አንደኛ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚወስደው የቅድመ ጭነት ብድር ዝቅተኛ ወለድ የሚከፈልበት በመሆኑ ሲሆን ሁለተኛ ምክንያት የተገኘውን የውጭ ምንዛሪ ያለገደብ እቃ ከውጭ ለማስገባት መጠቀም እንደሚችሉ ስለሚያውቁም ጭምር ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የመቆጣጠሪያ ስርዓት ክፍተት ያለው መሆኑ ነው፡፡

## 2.4. ለምርት ማጓጓዝ ያግዛል ተብሎ የሚሰጠው መኪኖች የማስገባት ዕድል

አዲስ የቅድመ ጭነት ብድር ሲፈቀድ ከዚህ ጋር ተያይዞ ለላኪዎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚሰጥ የጭነት መኪኖች ግዥ ብድር አንዱ ነው፡፡ ይህ ማበረታቻ አስፈላጊ ሆኖ እያለ አጠቃቀሙ ግን በትክክል የሚገመገም አይመስለኝም፡፡ አንደኛ የሚሰጠው ብድር በያመቱ ለተፈለገው ሥራ ከሚያስፈልገው በላይ በርካታ መኪኖች የሚያስገዛ ነው፡፡ ሁለተኛ እነዚህ መኪኖች የት ነው ያሉት ተብሎ ቁጥጥር አይደረግበትም፡፡ አንደኛና ዋነኛው ጉዳይ ያለው እነዚህ መኪኖች ለታለመላቸው ዓላማ አይውሉም ወድያውኑ ይሸጣሉ፡፡ ከነዚህ መኪኖች ሽያጭ የሚገኝ ትርፍ ከፍተኛ በመሆኑ ወደ ውጭ የሚሉኩዋቸውን እንደ ሰሊጥ፣ ቡና እና ሌሎች ጥራጥሬዎች በርከት አድርገው ገዝተው በኪሳራ ሸጠው በሚያሳዩት አፈፃፀም ብዛት ልኳል እየተባለ ሲሸለሙ ይታያል፡፡ ይህ አሰራር ኤክስፖርቱን በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳው እንደሆነ በግልፅ ሊታወቅ ይገባል፡፡

## 2.5. በኢትዮጵያ የምርት ገበያ/ንግድ ሚኒስቴር ያለው ሌላኛው ችግር

ሌላኛው የተቀመጠው አሰራር አንድ ላኪ አምራች ከሆነ ወደ ምርት ገበያ ሳያስገባ በቀጥታ ኤክስፖርት ማድረግ እንደሚችል እድል ተሰጥቶታታል፡፡ በዚህ አሰራር ላኪዎች ሌላ ኩባንያ በማቋቋም በማምረት ተሰማርተው እንደየሁኔታው ከፈለጉ በምርት ገበያ አስገብተው በውድ ዋጋ የሚገዙበትአልያም ዶላር የሚያስፈልጋቸው ከሆነም እንደሁኔታው ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ የሚገዙበትና በዝቅተኛ ዋጋ የሚሸጡበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህ ዓይነት አሰራር ምርቱ ባጠቃላይ ማግኘት ያለበት ትክክለኛ ዋጋ ሳያገኝ ከመቅረቱ በተጨማሪ አርሶ አደሮች ማግኘት ያለባቸው ጥቅም ሳያገኙ ይቀራሉ እንዲሁም በትክክለኛ መንገድ ከምርት ገበያ በትክክለኛ ዋጋ ገዝተው በትክክለኛ ዋጋ ለመሸጥ የሚፈልጉ ላኪዎች መንገዱን ቀርቅረው ይዘውባቸዋል፡፡

## 2.6. የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም

አስመጪዎች በርከት ያለ እቃ ገዝተው በጅቡቲ (Free Zone) በተካለለው ቦታ ሲያከማቹ የሚተማመኑት ዶላር በቀላሉ አግኝተው ንብረቱን ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይኸዉም የሚሆነው አንድ ላኪ የሚያገኘውን የውጭ ምንዛሪ ባንኮች ባመቻቸላቸው ክፍተት ለነፃ ቀረጥ መብት ላላቸው ድርጅቶች ለአንድ ዶላር እስከ 2.50 ብር ይሸጡላቸዋል፡፡ ይህ በመሆኑም ላኪዎች ከኤክስፖርት ቢከስሩ ዶላር በመሸጥ ሊያገኙት ስለሚችሉ ያላቸውን ብር ይዘው ቁጭ ከሚሉ በዚህ መልኩ ቢንቀሳቀሱ ይመርጣሉ፡፡

## 2.7. የቀረፅ ነፃ ባለመብቶች ወይም የኢንቨስትመንት ፍቃድ ያላቸው በተመለከተ

እነዚህ ግለሰቦች ትልልቅ ህንፃዎች፣ ሆቴሎች ወዘተ... እንገነባን እያሉ ከትልልቅ ከተሞች አልፈው የወረዳ ከተሞች በመሄድ ቦታ በመቀበል የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመያዝ ከቀረፅ ነፃ የኮንስትራክሽን ግብአቶች ከውጭ በማስመጣትና በገበያ በመሸጥ ከፍተኛ ትርፍ ስለሚያስገኝላቸው ከላይ እንደተጠቀሰው ዶላር ይገዛሉ ወይም ራሳቸውበወረደ ዋጋ Export በማድረግ ይሰራሉ፡፡ይህ የሚያሳየው መንግስት መዋእለ ንዋያቸው ለፈሰሱ ባለሃብቶች ማበረታቻ ማድረግ አለብኝ ያለውን ተገልብጦ መክፈል የሚገባቸው ቀረጥ ሳይከፍሉ ሃገር እየጎዱ ይገኛሉ፡፡

**የመፍትሄ ሃሳብ**

የውጭ ምንዛሪ ማግኘት በቀላሉ እቃን ከውጭ ለማስገባት ብቻ ሆኖ ትርጉም ሊሰጠው አይገባም፡፡ ይልቁንስ የመልካም አስተዳደር ጉዳይም ነው፡፡ ዜጎች በሃገራቸው ሰርተው ለመኖር ብሎም ለሃገራቸው የሚያበረክቱት አስተዋፅ ትርጉም ያለው እንዲሆን ከተፈለገ ፍትሃዊ የሆነ ክፍፍል ሊኖር ይገባል፡፡ ለመሆኑ ይህንን የሚስፈፅሙ አካላት እንዴት ያዩታል? ምንስ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

**1. የኢ.ፌ.ድ.ሪ ንግድ ሚኒስቴር**

የኢፌድሪ ንግድ ሚንስተር ወደ ውጭ የሚልኩትን ምርቶች  እንዲከታተል ስልጣን የተሰጠውአካል በመሆኑ በየዓመቱ ከላኪዎች የጋራ መሪ እቅድ በማውጣት ከኤክስፖርት ምን ያክል የወጭ ምንዛሪ እንደሚገኝ ያስቀምጣል፡፡

ይህ ሲያደርግ የመቆጣጠርያ ስርዓት ብሎ የሚያስቀምጠው ትልቁ መሳርያ ከገዢዎች የታሰረው የገዥና ሽያጭ ውል መፈፀሙና አለመፈፀሙ እንዲሁም የክምችት መጠን በላኪዎች እጅ ምን ያህል ነው የሚል ነው፡፡ ንግድ ሚኒስቴር ለበርካታ ዓመታት አሻግሮ ያላያቸው ወይም እያያቸውም በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈታቸው ያልፈለገ ነገር ግን በተደራጀ መልኩ ስርዓት ሊያፈርሱ የሚችሉ ተግባራት እየተፈፀሙ ስለሆነ ቢያንስ ባሁኑ ግዜ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል፡፡

1. ንግድ ፍቃድ ለሚያወጡ ዜጎች የሚጠየቀው የብቃት መረጋገጫ ጠንከር ቢል
2. ንግድ ሚንስቴር የመቆጣጠሪ ስርዓቱ እንደገና ቢፈተሽ የሚመዘገቡት ውሎች የምርቱ ትክክለኛ ዋጋ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. የኩባንያዎች ትስስር በደንብ መጠናት ይኖርበታል፡፡ አንድ ኩባንያ እህት ኩባንያ ካለው በምን ዘርፍ የተሰማራ መሆኑና ከሌላኛው ኩባንያ ምን ዓይት ትስስር አላቸው የሚል ቢታይ
4. አንድ ግለሰብ በስሙ ድርጅት ካለው በባለቤቱ የተከፈተው ድርጅት ሌላ ድርጅት በምን ዘርፍ እንደተሰማራ ቢፈተሸ

**2. የኢትዮጵያ ቢሄራዊ ባንክና ንግድ ባንኮች**

የኢትዮጵያ ቢሄራዊ ባንክ በተለይ በቡና ሽያጭ ቁጥጥር የሚያደርግ አካል ነው፡፡ የግዥና ሽያጭ ውል የሚመዘገበው በዚህ ባንክ ነው፡፡ እንደ አሰራር አንድ ሽያጭ በወሩ ከተሸጠው አማካይ ዋጋእስከ 10% ዝቅ ብሎ የሸጠ ማንኛውም አካል አይጠየቅም፡፡ ከ10% በላይ ዝቅ ብሎ ቢሸጥ ይጠየቃል ይላል፡፡ ይህ አሰራር በርካታ ክፍተቶች አሉት፡፡

1. ግለሰቡ ወይም ኩባንያው የሚጠየቀው ሽያጩ ከተከናወነ ከወራት በኋላ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም የሚነገረው ያለፈ ታሪክ በመሆኑ፡፡

2. 10% ማለት በጣም ትልቅ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ቶን ቡና 3000 የአሜሪካን ዶላር አማካይ ዋጋው ቢሆን አንድ ላኪ 300 ዶላር ዝቅ ብሎ ቢሸጥ ችግር የለዉም፡፡ ይህ መጠን ልዩነት በትክክል ለመነገድ የሚያስቡ ድርጅቶች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ አይፈጥርም፡፡

3. አንድ ላኪ ከ10% በላይ ዝቅ ብሎ ሸጦ ማስጠንቀቅያ ቢደርሰዉም ላኪው በሚያቀርበው አስረጂ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ይሻራል፡፡ ይህ አሰራር ጠንቅቆ የሚውቅ ላኪ ክፍተቱን በደንብ ይጠቀምበታል፡፡

ስለሆነም ባንኮች ከተለያዩ ምንጮች መረጃ በማሰባሰብ የግዥና የሽያጭ ውሎች ወዲያውኑ ሲመዘገቡ ከዋጋ በታች ነው ብለው ቢሰረዙ የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሌላው የኢትዮጵያ ብርዊ ባንክ መፍታት ያለበት ችግር የውጭ ንዛሪ ክፍፍሉ ፍትሃዊ እንዲሆን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚተገበረው መመርያ በግል ባንኮች እንዲተገበሩ መቆጣጠር ይኖርበታል፡፡

## 3. የኢ.ፌ.ድ.ሪ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

የሃገራችን የእርሻ ውጤቶች ተገቢውን ዋጋንና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገኙ ከተፈለገ ባለሃብቶች ወደ እሴት የመጨመር ስራ እንዲገቡ ከፍተኛና አፋጣኝ የሆነ ተጨባጭ ስራዎች መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ከተደረገ የገበያ እድል ይሰፋል፡፡ ላኪዎች ከፍተኛ የትርፍ ህዳግ ስለሚያገኙበት አስፈላጊ ወዳልሆነ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር አይገቡም፡፡

## 4. የኢንቨስትመንት ፍቃድና የነፃ ቀረፅ መብት

ይህንን ተከታትሎ የሚያስፈፅም አካል ከሚመለከታቸው አካላት በመሆን በነፃ ቀረፅ መብት በኢንቨስትመንት እንጂ ለንግድ መዋል እንደሌለበት ግልፅ ሆኖ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

## 5. የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም

አንደኛ ላለ አገር የውጭ ምንዛሪ ክምችት/አቅርቦት ችግር ባለበት ሁኔታ ጥብቅ ቀጥጥር በድልድሉ ይሁን በአጠቃቀሙ ሊደረግበት ይገባል፡፡ በአገራችን ያለው ፈጣን ዕድገት ወሳኝ ተራ የሚጫወተው የውጭ ምንዛሪ ግኘት እና አጠቃቀሙ ላይ ስለሆነ ለዚህ መንግስትና ባንኮች ልዩ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡